*ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ*

*Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity*

Efdpu@aol.com www.Finote.org

*ፕሮግራም፣ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 25 ሜትር ባንድ*

*Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on 25 meter band*


***የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ***
***ታህሳስ 27 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ***

# <u>ግቡን ያልመታ ዓላማ ፤</u>

# <u>ሂደቱን ያላገባደደ ትግል</u>

በመርኅ ፅናት፤ በራስ መተማመን፤ በሀገር ፍቅርና በሕዝብ ወገንተኝነት ላይ የተመሰረተ የነጻነት ትግል፤ ፈጠነም ዘገየ ግቡን መምታቱ አይቀሬ ነው። በዓላማ ፅናት ላይ የተመረኮዘ ትግል ድልን መጎናጸፉ አጠራጣሪ አይሆንም። ይህ ደግሞ አፍ እንዳመጣ የሚነገር ሳይሆን፤ በታሪክ ተበጥሮ የተመሰከረለት ሀቅ ነው። ለአለፈው ግማሽ ምዕተ-ዓመት፤ በሀገራችን፤ ሁለት ተጻራሪ ኩነቶች አልተለወጡም ። አንደኛው የአምባገነን ሥርዓት፤ መልኩን እየለዋወጠ ተንሰራፍቶ መቀጠሉ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ፤ ተዳፍኖ ያልተዳፈነው የሕዝብ አመጽ ነው። እነኝህ ሁለት ተጻራሪ ኃይሎች ተጻርረው እስከቆሙ ደረስ፤ ትግል መቀጠሉን ይቀጥላል። ጭቆናና አመጽ በባኅሪያቸው፤ አጥፊና ጠፊ ሰለሆኑ፤ በአንድ ሀገር ተስማምተው ሊኖሩ አይችሉም። ጨቋኙ ሥርዓት እየተጠራሞተ ሲቀጥል፤ የህዝብ አመጽ በበኩሉ፤ እየተከላወሰም ቢሆን ትግሉን ያራምዳል። ይህንን ሁኔታ በማያዳግም መልኩ ሊለውጥ የሚችለው ግን፤ የኀይል ሚዛኑ ወደ ሕዝቡ አመፅ ሲያጋድል ብቻ ይሆናል ።

"ፖለቲካ፤ ሊሆን የሚችለውን የማየት ጥበብ ነው " ( ዘ አርት አፍ ፖሲብል ) እንዲሉ፤ የሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ የሚያመለክተው ሃቅ ቢኖር፤ በጊዚያዊ ደረጃም ቢሆን፤ የኀይል ሚዛኑ ለወያኔ ያጋደለ መሆኑን ነው። ይህንን ሃቅ መረዳት፤ ደግሞ የጠላትን ማንነት በሚገባ ተገንዝቦ የራስን አቅምና ሁኔታ ገምግሞ፤ ኃይልን አሰባስቦና ኣጠናክሮ እንዲታገሉ ይረዳል። የውጊያ፤ የመጀመሪያው ዕውቀት፤ የጠላትን ምንነት በሚገባ መረዳት እንደሆነ ማንም ተዋጊ፤ ሊስተው የሚገባ ጉዳይ አይሆንም። ይህንን አለመረዳት፤ በሀገራችን ከተመከሮ እንደምንገነዘበው የዕርሻን ማሳ በበሬ ቀርቶ፤ በአህያ እንደ ማረስ ይቆጠራል። በአህያ የታረሰ ዕርሻ ደግሞ፤ ምን እንደሚመስል፤ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያደገ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያውቀዋል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ዛሬ የሚታገለው ከወያኔ ጋር ብቻ ሳይሆን፤ ከበላይ ጠባቂዎቹ፤ ከባዕዳን ኃይሎች ጋርም ጭምር ነው። በመሆኑም፤ የኃይል ሚዛኑ ለወያኔ እያጋደለ እንዲቆይ አድርጎታል። ይህንን ሚዛን መለወጥ አይቻልም ማለት ግን አይደለም። በግድም ሆነ በውድ ይለውጣል። ማን ነው የሚለውጠው? እንዴትስ ሊለወጥ ይችላል? ሁኔታውን ለመለውጥ ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል? እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች መመለስ ግን እታገላለሁ ለሚለው ሁሉ ግዴታ ይሆናል ።

" ዝምብ ቢጠራቀም ወስከምቢያ እንዳማይከፍት " ሁሉ፤ ጉተና (ጎፈሬ) አሳማሪው ሁሉ ዐርበኛ ሊሆን አይችልም። ለዚህም እኮ ነበር " አንዳንድ ዋልጌ አይጠፍም ጉተና አሳማሪ፤ ሲሄዱ በኋላ ሲመለሱ መሪ "

ተብሎ በአርበኞች የተዘመረው ። "የሚያንጸባርቀው ሁሉ ወርቅ እንዳልሆነ" ሁሉ፤ የድርጅት ደግሰ ወጥ ቀማሽ የሆነው ሁሉ፤ ዕውነተኛ ታጋይ ነው ማለት አይደለም። በተመክሯችን፤ የኃይል ሚዛኑ ወደ አደላበት ጥብቆውን የሚቀያይረውን ሁሉ ለመገንዘብ ችለናል። በቅርቡ ፈትልኮ እንዲወጣ ከተደረገው፤ በ 168 ገጽ የተጠናቀረ ሰነድ ከተገኘው መረጃ እንደተዘረዘረው ፤ ቁጥራቸው 169 የሆነ፤ በዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን እና የንግድ ተቋማት የወያኔ ግብረ-በላዎችና ተባባሪ እንደሆኑ አጋልጧል። ከእነኝህ መካከል በሦስቱ ተፈራራቂ መንግሥታት፤ ማለት በዐጼ ኃይለ ሥላሴ፤ በደርግና በወያኔ አምባገነን ሥርዓቶች ያገለገሉና የተጠቀሙ ግለሰቦች አሉበት። ሕዝብንና ሀገርን እየከዱ ለሚመጣው ሁሉ ጋሻ ጃግሬ ሆኖ ማገልገል የነበረ፤ ያለና ወደፊትም የሚኖር ስለሆነ የሚያስደንቅ ሆኖ አላገኘነውም ።

በያንዳንዱ 12 ሐዋርያት አንድ አንድ ይሁዳ መኖሩ ጥንትም የነበረ ነው። ወደፊትም፤ የህብረተሰብ መኖር እስከቀጠለ ድረስ ይህን ዓይነት ክስተት መቀጠሉ አይቀርም። ጉዳዩ ይህ ቢሆንም፤ በአሁኑ ወቅት እጅግ አሳሰቢ እየሆነ የመጣው ሁኔታ ግን፤ ለአላፊ- ጠፊ ጥቅም ሲባል፤ ወገንን በመሰለልና ትግሉንም በመጉዳት ላይ የተሰማሩት ከሃዲያን ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ ነው ። ይህ ጉዳይ በቀላሉ ሊታይ አይገባም። ሀገሩን፤ ከወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ነጻ ለመውጣት የሚፈልገው የህብረተስብ ክፍል፤ እራሱን ከወያኔ ሰላዮችና ከፋፋዮች መከላከል አለበት ። ይህንን ካደረገ የኃይል ሚዛኑን፤ በማያጠራጥር መልኩ ወደ ትግሉ ሊያዝነብልለት ይችላል።

እኔን ከጣመኝ ለሌላው ምን አገባኝ ማለት የሰብዕና ምልክት አደለም። ትላንት፤ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ያስገነጠለው ሻዓቢያ፤ "ባኀላይ አይትኹሁን ንዓይ ይጥዓመኒ ! " ለእኔ ይጣመኝ ባይ አትሁን " የሚል ዘፍን እያሰማ ነበር ህዝቡን ሲቀሰቅስ የነበረው። በእኛው መከከል ግን፤ እኔን ከተመቸኝ ለሌላው ምን አገባኝ የሚለው ቁጥር እየበረከተ ይገኛል። በሀገር ቤት፤ የከተማ ቦታ ገዝቶ ቤት ማሰራት፤ የገጠር መሬት በመመራት እርሻ ለማረስ መሯሯጥ ለሀገር ኀልውና የማስብን ህሊና በክሎታል። ይህ ቁጥር ደግሞ ለአጭር ጊዜም ቢሆን፤ የኃይል ሚዛኑን ወደ ወያኔ ያጋድለዋል። የስበቱን ማዕከል ( ሴንተር ኦፍ ግራቪቲ ) ወደ ተቃዋሚው ጎራ እስካላመጡት ድረስ፤ የኃይል ሚዛኑን ማግኘት አይቻልም። ዘረኛው ሥርዓት እየቀጠለ፤ የሀገሪቱ መጥፋት እርምጃ እየተፋጠነ ይሄዳል። ትላንት ኤርትራ ስትገነጠል ዋይታና ለቅሶ እንደተደረገው ሁሉ፤ ነገ ኢትዮጵያ ከጠፋች በኋላ፤ ያዙኝ ልቀቁኝ ማለቱ ለማንም አይጠቅምም።

አሁኑ ከተደረሰበት ደረጃ ሲታይ፤ አያሌ ሁኔታዎችን መገምገም ግድ ይላል። የትግሉን አቅጣጫና ፍጥነት ወደፊት ለማራመድ ካስፈለገ፤ በወያኔ ወንጀልና ጥፋት ላይ ማተኮሩ ብቻ በቂ አይደለም። የወያኔን ሀገራዊ ወንጀልና ጥፋትማ፤ ከደቂቅ እስከ ሊኀቅ ሁሉም ዜጋ አውቆታል፡፡ ተገንዝቦታል። ውግዘቱ፤ ርግማኑ፤ መኮነኑ፤ ተቃውሞው ጥላቻው ወዘተ.. ሁሉ ቢደረደር፤ ብቻውን በቂ እንዳልሆነና ሥርዓቱንም ሊያነቃንቀው እንዳልቻለ ገልፅ ከሆነ ቆይቷል። ሥርዓቱ፤ ከስር- መሠረቱ እንዲነቀል ከተፈለገ፤ የሚከተሉትን ዐበይት ጉዳዮች በቅደም- ተከተል እየገመገሙ፤ ሁኔታውን ለመለወጥ ትግሉን ከማጠንከር ሌላ አማራጭ አይኖርም። ትግሉ ግቡን እንዲመታ ከተፈለገ፤ የሕዝቡን ልብ ትርታ ማውቅ አስፈለጊ ነው ብለን እናምናለን። ይህ ማለት ፦

ሀ) ዛሬ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመቸውም በበለጠ መስማትና ማየት የሚፈልገው፤ የተሻለ አማራጭ ዕቅድና ሀገራዊ ፕሮግራም ይዞ የሚመጣለትን ኃይልና ደርጅት ብቻ ነው ።

ለ) የዚህ ሀገራዊ አማራጭ ኃይል ሆኖ ለመምጣት/ ለመውጣት ደግሞ ሁሉ- አቀፍ አመለካከትን፤ ስትራተጂያዊ ራዕይንና፤ ሁሉንም የሚያስተባብር ማዕቀፍ መኖር የግዴታ ነው። በመሠረታዊ ይዘቱና ባህሪዩ፤ ከወያኔ የተሻለ የመንግሥት ተቋም በአማራጭ ይዞ መቅረብ የሕዝቡን ድጋፍና ይሁንታን ሊያስገኝ ይችላል ።

ሐ) የፖለቲካው ርዕዮት፤ የኢኮኖሚውን ሥርዓት፤ የሀገሪቱ አስተዳደራዊ አወቃቀር፤ ምን አይነት ፌዴራላዊ ሥርዓት መሆን ይገባዋል? የሚለው መሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄ መልስ ማግኘት አለበት።

መ) የመሬቱ ስሪትና ይዞታ፤ የግለሰብ መብት መከበርና የህብረተሰብ ነፃነት፤ ሁሉ ከወያኔ የተለየና የተሻለ መሆኑን እንዳማራጭ ይዞ መቅረብን ሕዝቡ ይጠብቃል። በአይነታው፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በእርሻ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፤ መሬት ከመንግሥት ይዞታ ወጥቶ ለሕዝብ በይዞታ/በባለቤትነት መተላለፍ አለበት። ይህም ማለት፤ ማንም ዜጋ፤ መሬትን የመጠቀም፤ የማውረስ፤ የመሸጥ በወለድ -አገድ የመያዝ/ የማሲያዝ ወዘተረ መብቱ ሊከበርለት ይገባል ማለት ነው። "መሬት ለአራሹ!" የሚለው የሕዝብ ጥያቄ፤ መሬትን ለሕዝብ እንጅ ወደ መንግሥት ቁጥጥር ይዘዋወር የሚል አልነበረም። ኢትዮጵያዊ አመለካከት ያልነበረውና አሁንም የሌለው ወያኔ ግን የህዝብን ጥያቄ አፍኖ መሬትን በቁጥጥሩ ስር ብቻ ሳይሆን ገበሬውንም የግሉ ጭሰኛ አድርጎታል።

ሰ) የሀገሪቱ የውጭ መመሪያ፤ የመከላካያና የብሄራዊ ጸጥታ ፖሊሲ፤ የህግና ደንብ አስከባሪ ተቋማት፤ የፖሊስ ሠራዊት አወቃቀርና አስተዳደር፤ የፊናንስና የባንክ፤ የጉምሩክ አስተዳደር፤ የውጭ ንግድ ፖሊሲ፤ የትምህርት፤ የጤና፤ የፍትኀ-ርትዕ ይዞታና መከበር፤ ሀገራዊ ሀብትን የመጠበቅ፤ የተፈጥሮ ሀብትን፤ ያካባቢ ብክለትን የመከላከል ፖሊሲን ሁሉ በጥቅልና በዝርዝር ተመዝግቦ እንደ አማራጭ ሊቀርቡ ይገባል። ሕዝቡም በአንክሮ ይጠብቃል።

ረ ) የዚህ ሁሉ መሠረትና አልፋ-ኦሜጋ፤ ሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ህገመንግሥት የማግኘትና በዚያም የመተዳደር ጉዳይ ነው። ለዴሞክራሲ ሥርዓት መሠረትና ምሰሶ ደግሞ አምባገነን እንዳያቆጠቁጥ ለመከላልከል የሚያስችሉ ተቋማትን መመስረት ነው። እነርሱም፡---

1ኛ፣ የመንግሥት ሥልጣን በአንድ ፓርቲ ቁጥጥር እጅ እንዳይገባ፤ የሃይል ክፍፍልና ቁጥጥር በሚዛን ማስቀመጥን ይጠይቃል። ነጻ ምክር ቤት መኖሩ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ነው።

2ኛ. ከማንኛቸውም መንግሥታዊ አካላትና ተቋማት፤ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥጥር ነጻ የሆነ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ነጻነት ዋስትና ይሰጣል።

3ኛ. የነጻ ፕሬስ መኖር፤ ለሕዝብ የሚያስገኘው የሃሳብ ነጻነት ዋስትና፤ ስሉስ ( ሦስት) ምሶሶዎች ለሚዛንና - ለቁጥጥር መረጋገጫ ይሆናል። የማንኛውም ሀገር ሕዝብ ማመን/ መተማመን የሚችለው እራሱ በሚመሰርተው ተቋም እንጅ በግለሰቦች ላይ ሊሆን አይገባም።

4ኛ. በአንድ ሀገር፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሚያስተማምን መልኩ ስር ሰድዷል ለማለት የሚቻለው፤ አርባዓቱ ( አራቱ ) ነፃ ተቋማት በነጻ ተመስርተው፤ ተግባራቸውን በነፃነት ሲያከናውኑ ነው። በህግ

ተደንግጎ በሚሰጣቸው መብትና ግዴታ ሙያቸውን ሲፈፅሙ ብቻ ነው። እነኝህ አራት ምሶሶ የሚባሉት ፦ ሀ) አስፈጻሚው ዘርፍ ለ) የህዝብ ምክር ቤት 3 ) የዳኝነት ክፍሉ ( ፍርድ ቤትና 4ኛ) ነጻ ፕሬስ ናቸው ። እነኝህ ተቋማት ነጻ ሆነው መመስረትና በነጻነት መስራት አለባቸው ። ይህ ካልሆነ፤ ሕዝብ ከአምባገነኖች ጭቆና ነፃ ሊሆን አይችልም ።

እስካሁን እንደተገነዘበው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ መተማመን ያለበት፤ ሊቆጣጠራቸው በሚችላቸው ታቋማት እንጅ በግለሰቦች ማመን እንደሌለበት በሚገባ ተረድቷል። ለራሱ ነፃነት ዋስትና መገኘት ከራሱ በላይ ማንም ሊሆን አይችልም። በህግ የተደነገገ ስምምነት (ኮንትራት ) እንጅ፤ ከእንግዲህ ወዲህ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪዎችን ማመን አይችልም። ተጠያቂትና ኃላፊነት ተጣምረው ካልተያዙና **ማንኛውም ሰው ከህግ በላይ አይደለም፤** የሚለው ብሒላዊ የፍልስፍና አነጋገር ቦታ ተስጥቶት ካልተከበረ፤ በተግባር እንዳየነው ማንኛውም አምባገነን ወጠጤ እየመጣ ሀገር አጥፍቶ ይጠፋል ።

ከላይ የተዘረዘሩት ሀገራዊ አማሮጮች በተቃዋሚው ጎራ በኩል በኅብረት ተዘጋጅተው አልቀረቡለትም። ይህ ሁኔታ ዕውን እስካልሆነ ደረስ ደግሞ፤ አንቃር እስኪሰነጠቅ ድረስ ጨቋኙን ሥርዓት ቢያውግዙት ብቻውን መፍትሄ አያስገኝም ። አንድ የማይካድ ሀቅ አለ። ይኸውም፤ ከሃያ አራት ዓመት መራራ አገዛዝ በኋላ፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በወያኔ ላይ ያለውን ተቃውሞ የመሠረተው በሚከተሉት ዓይነተኛ ምክንያቶች ነው ።

1ኛ. በዘርና በቋንቋ ላይ የተመሰረተ የመንግሥት ሥርዓት ህዝብን ከፋፋይና ሀገር አጥፊ በመሆኑ አንቅሮ ተፍቶታል።

2ኛ. የዴሞክራሲ መብቶች ጠፍተው አምባገነናዊ አገዛዝ በመስፈኑ፤ አንድ- ለአምስት በሚሉት የፀጥታ ማዕቀፍ የተዋቀረና የህዝቡን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚቆጣጠር አፋኝ መዋቅር ዘርግተው አሸባሪና አስፈሪ ሥርዓት መዘርጋታቸው፤

3ኛ. የውጭ ጉዳይ ፖሊሲው የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ያስደፈረ፤ አዋራጅና ለባዕዳን ተንበርካኪ በመሆኑ፤ ይህም፤ ኢትዮጵያን ለዳግም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የዳረጋት በመሆኑ የሕዝቡን ተቃዉሞ ይበልጥ አጋግሎታል።

4ኛ. የኢኮኖሚው ሥርዓት ጊዜው ያለፈበት፤ የዕዝ ኢኮኖሚ ( ኮማንድ ኢኮኖሚ) በመሆኑ፤ በጣት የሚቆጠሩትን የወያኔ ተባባሪዎች በሚያስገርም መልኩ ሲያበለፅግ፤ ምልአተ - ሕዝቡን በድህነት አረንቋ ውስጥ አስገብቶታል። ልማታዊ መንግሥት ነኝ በሚል ፕሮፓጋንዳ ሕዝቡን በእርጎ ባህር ውስጥ ለማስዋኘት ይሞክራል። ድኅነትንና ችግርን በአጉል ፕሮፓጋንዳ ቢደልሉት፤ በረሃብ የተኮማተር አንጀት ጎኑ አይጠገንም ።

" ራበኝ ርሃቡ ጎኔን ጎኔ ወጋው፤ አፅሜም ፈጥጦ ወጣ፤

ልማታዊው መንግሥት እንጀራ ላያስገኝ፤ ዳቦ ላያመጣ ፤

መቼም አለቀቀኝ መከራና ጣጣ፤ ደርግን አስወግጄ ወያኔም ቢመጣ፤

ተተክቶ ገባ የሕዝብ ከፋፋይ፤ የሀገር ባላንጣ፤ ውሸታም ዐይን አውጣ፤

ከመከራው ኑሮ፤ እንዴት ብየ ልሸሽ፤ ልሰደድ፤ ልኮብልል፤ ከዚህ ስቃይ ልውጣ !

በእርጎ ባህር ልዋኝ ? ራሴን ልደልል ? ፤ በተስፋ ልዝናና ?

እንጀራስ በሽሮ አይገኝምና ውርደቱ ቀርቶልኝ ጎመኔን በጤና

ልጄም ተሰደደች ለአረቦች ግርድና ፤ ለውርደት ልመና

ሀፍረቷን ሳትሸሽግ ሳትደብቅ ገመና፤ አንገቷን ደፍታለች ፤ ሳይኖር ስብዕና ፤

ታሪክና ባኅል፤ ሀገርና መንግሥት፤ ሕዝብ ሆነ አርበኛ፤ ጀግናም ጠፍቷልና !

እያለ ምሬቱን በመግለፅ ሥርዓቱን ይቃወማል። ይህ ደግሞ የወያኔ ወድቅ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ውጤት ነው።

5ኛ. በጠብመንጃ አፍ- ሙዝ ተከብቦና በወያኔ ድርጅት አበጋዝነት የተጻፈ ህገመንግሥት፤ የሀገሪቱን ሕዝብ ፈላጎትና ዓላማ የሚጻረር በመሆኑ፤ ማንም ዜጋ አክብሮትና ተቀባይነት አልሰጠውም። የአንድ ብሄር የበላይነትን የአረጋገጠ ሰነድ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደሚውክል ሆኖ ሊቆጠር አልተቻለውም። ከጥንስሡ- እስከ አረቃቀቁ ሂደቱና አጸዳደቁ ድረስ፤ የሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ ያልነበረው በመሆኑ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባዕድ ነው። ተቀባይነትም እንደሌለው፤ ሕዝቡ ባገኘው አጋጣሚው ሁሉ ተቃዉሞውን ሲያሰማ ኖሯል። ይህ ሁኔታ የኢትዮጵያን ሕዝብ፤ ልክ " **ዐይነ ስውር፤ በጨልማ ቤት፤ ጥቁር ባርኔጣ እንደሚፈልግ** " አስመስለውታል ። አሹፎበታልም። በጽልመት ውስጥ ከተጋረደ የወያኔ ህገ አገዛዝ፤ ዴሞክራሲ ሰፍኖልሃል ብሎ ማለት፤ ቢያንስ የሕዝቡን የአዕምሮ ብስለት ( ኢንተለጀንስ ) መስደብ ይሆናል ።

ከላይ በተዘረዘሩት አምስት መሰረታዊ ምክንያቶች፤ ወያኔ ከነሥርዓቱ መወገድ እንዳለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወሰነ ቆይቷል። ውሳኔውን ወደ ተግባር ለመለወጥ ግን አንድ በር መከፈት አለበት። ይኸውም በተቃዋሚው ጎራ የተዘጋጀ ከወያኔ የተሻለ አማራጭ ሥርዓተ- መንግሥት ዕቅድ ለኢትዮጵያ ማቅረብ ነው። ይህ አማራጭ በላይኛው ገጽ፤ ከፊደል ተራ ሀ እስከ ረ ድረስ ተዘርዝሯል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የወደፊቱ ብሩኅ ተስፋ፤ ዓላማውን እንዲመታ፤ ብሎም፤ ትግሉ በአቸናፊነት እንዲገባደድ ከተፈለገ፤ የተቀነባበረ ሀገራዊ አማራጭ ይዞ መቅረብ፤ ወቅታዊና አንገብጋቢ መሆኑን ሁሉም ሊረዳው ይገባል እንላለን ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !